Freebirtukan.org

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

## የብርቱካን ሚደቅሳን መታሰር በመቃወም የሻማ ማብራት በመስቀል አደአባይ እንዳይደረግ ኢሕአዴግ መከልከሉን በተመለከተ የወጣ መግለጫ !

ታህሳስ  19 ቀን 2002 ዓ.ም

የኢሕአዴግ አገዛዝ ታህሳስ 20 ቀን 2001 ዓ.ም የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን፣ ኢፍትሃዊና ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ በአሥር የደህንነት አባላት እየተዋከበችና እየተንገላታች ወደ ቃሊት እሥር ቤት እንድትሄድ እንዳደረገ ይታወቃል። ይህንንም በመቃወም በአገር ቤትና በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የአለም አቀፉ ማህብረሰብ ያለውን ተቃውሞ ሲያሰማ ቆይቷል። አሁንም እያሰማ ነው።

የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የወሰዱት እርምጃ ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት እንደሌለውና ሙሉ ለሙሉ የሕግ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን «የሕግ ጉዳይ ነው» ቢባልም የሚቀርቡት የሕግ መከራከሪያዎች ግን እዚህ ግቡ የማይባሉ ናቸው።

እንደውም ሕግን የሚረግጡ ሕግ የሚጥሱ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት መሆናቸውን በገሃድ እያየን ነው።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችበትን አንድ አመት ለማስታወስ፣ መታሰሯ ሕገ ወጥ እንደሆነ ለማሳወቅና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ መፈታቷን ለመጠየቅ፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ሊደረግ ታቅዶ የነበረው የቃሌ ሻማ ማብራት ዝግጅት፣ በአዲስ አበባ አስተዳደር ያሉ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ፍቃድ መከልከላቸው ብቻ እንደ አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የአገሪቷ የበላይ ሕግ ነው። በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 30 የሚከተለውን እናገኛለን፡

*«ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጠሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ  ወይም ሰላማዊ ሰልፍ  ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብ የሞራል ሁኔታ ለማስጠበቅ አግባብ ያሉ  ሥርዓቶች ሊደነግጉ ይችላሉ»*

በዚህ አንቀጽ፣ ዜጎች በሰላማዊ መንገድ እስከሆነና የጦር መሳሪያ እስካልያዙ ድረስ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ሙሉ መብት እንዳላቸው በግልጽ እናያለን።

ገዢው ፓርቲን ጨምሮ አራት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የ2002 ዓ.ም ምርጫን በተመለከተ ያዘጋጁትን የምርጫ ሥነ-ምግባር ሰነድ፣ ከጥቂት ወራት በፊት በአዲስ አበባ ሼራተን መፈራረማቸው ይታወሳል። እነዚህ ፓርቲዎች ያዘጋጁት የምርጫ ስነምግባር ሰነድ በአገሪቷ ፓርላማ ጸድቆ ከጥቂት ቀናት በፊት «የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ-ምግባር ለመደንገግ የወጣ አዋጅ» በሚል ስያሜ ሕግ ሆኖ ወጥቷል።

በዚሁ ሕግ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2.መ የሚከተለውን እናገኛለን ፡

Freebirtukan.org

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

“ *አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ሰፊ የሕዝባዊ ድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባዎች ወይም የእግር ጉዞና ሰላማዊ ሰልፎች እንዳያደርግ ማገድ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ የለበትም»*

በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2.ረ ደግሞ ፡

> *“አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈጽሙ መፍቀድ የለበትም»*

የሚል ተጽፎ እናነባለን።

ከላይ በግልጽ በተቀመጠዉ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ እንዲሁም በሰፊዉ እንደ ትልቅ ክንዋኔ ሲነገርለት በነበረበዉ በምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ በሰፈሩት ሕግጋቶች መስረት፣ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በግፍ መታሰርን፣ በሰላማዊ መንገድ ለመቃወምና በመስቀል አደባባይ የቃሌ ምሽት የሻማ ማብራት ሥነሥርዓት ለማድረግ ፍቃድ የጠየቁ ኢትዮጵያዉያን ፍቃድ ሊሰጣቸዉ ይገባ ነበር። እነዚህ ኢትዮጵያዉያን መሳሪያ ሳይሆን ሻማ ለመያዝ የተነሱ፣ ሰላማዊ ኢትዮጵያውን እንደመሆናቸዉ በማናቸዉም የሕግ መስፈርትና መመዘኛ የሚከለከሉበት ምክንይት አልነበረም።

በመሆኑም ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያለዉን ክብርና ፍቅር በመስቀል አደባባይ እንዳያሰማ መከልከልሉ በእጅጉ ያሳዘነንና የምናወግዘዉ መሆናችንን እንገልጻለን። ዉሳኔዉ ሕገ መንግስቱን የናደ ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ የተፈረመዉንም ሰነድ ወረቀት ብቻ እንደሆነ ያሳየ ነዉ።

አቶ መለስ ዜናዊ ለአገር ዉስጥ ጋዜጠኞች በቅርቡ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከቃሊቲ እሥር ቤት እንደማትወጣ መናገራቸዉ ይታወሳል። ነገር ግን ይህ አይነቱ የአቶ መለስ አነጋገር ከማንም የበለጠ የሚጎዳዉ ኢሕአዴግን እራሱ ነዉና፣ አቶ መለስም ሆነ የሥራ አጋሮቻቸዉ ቆም ብለዉ በአገራችን ያለዉን ሁኔታ እንዲያገናዝቡ፣ የሕዝቡን ስሜት እንዲመዘኑ ያስፈልጋል ባዮች ነን። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በእሥር ቤት ባቆይዋትም መጠን አቶ መለስና ድርጅታቸዉ የበለጠ የፖለቲካ ተቀባይነታቸዉ እያሽቆለቆለ የሚሄድ መሆኑንም በርግጠኝነት ማወቅ ይኖራባቸዋል እንላለን።

ኢሕአዴግ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በማሰሩ አንዳችም ጥቅም እንደማያስገኝለት እየገለጽን፣ ይችን ታላቅ ሴት ለራሱ ሲል በአስቸኳይ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ እንጠይቃለን።

አገራችን ኢትዮጵያ ሰላም ያስፈልጋታል። የምርጫ ሥነ-ምግባር ሰነድም ሆነ ማናቸዉም አይነት ወረቀቶች ሰላም አያመጡም። ሰላም እንዲኖር ብሄራዊ እርቅ መምጣት አለበት። ብሄራዊ እርቅ እንዲመጣ በጎ መንፈስ በሁሉ ወገን እንዲፈጠር ያስፈልጋል። በጎ መንፈስ እንዲፈጠር በቀዳሚነት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች በርካታ የሕሊና እሥረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ የግድ ነዉ።

ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች የሕሊና እሥረኞች አሁን ይፈቱ !